# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 337 ጥቅምት 15 2007


የመከላከያ ሠራዊት አባላት በኑሮም በዘረኝነትም እየተማረሩ ነው፤ አለቆቻቸው ግን አሁንም በዝምድና እየተፈላለጉ እየተሿሿሙ ነው። አሁንም በዝምድና እየተፈላለጉ እርስ በራሳቸው እየተሿሿሙ ጄኔራሎች ሁሉ ዘመዳሞች ሆኑ፤ በሥራቸው ያለውን ኢትዮጵያዊውን ወታደር ግን እንደ ግል አሽከራቸው እንኳን ማየት ተጠይፈዋል። በጄኔራሎችና በሠራዊቱ መካከል ያለው ግኑኝነት ከጌታና ሎሌም የባሰም ሆኗል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የወያኔ ዘረኞች በአማራ ተወላጆች ላይ የከፈቱትን ዘመቻ አሁንም እንደቀጠለበት ነዉ

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ከሁለት አስርተ አመታት በላይ በአፋር ክልል በተለያዩ ሞያዎች ተሰማርተው ሲሰሩ የቆዩ ቁራቸው ቀላል የማይባል የአማራ ብሄረሰብ ተወላጅ ኢትዮጵያውያንን ክልሉን በአስቸኳይ ለቃችሁ ውጡ ሲል ትዕዛዝ ማሳለፉን ለማወቅ ተችሏል። ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ለዘመናት በፍቅር ተስማምተው፤ ተጋብተውና ተዋልደው እየኖሩ የሚገኙት እነኝሁ ኢትዮጵያውያን በአገዛዙ በተላለፈው ቅጽበታዊ ትዕዛዝ መረበሻቸው ታውቋል። ትዳራችንንና ልጆቻችንን በትነን ወደ የትም አንሄድም ሲሉ አገዛዙን እየተማጸኑ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ቢኖሩም ከዘረኛው ህወሃት የክልሉ ጭፍሮች በየ ዕለቱ በሚደርሳቸው ዛቻና ማስፈራሪያ የተነሳ በፍርሃት ድባብ ተውጠው እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል። ኢትዮጵያውያኑ የተቃውሞ ደብዳቤ ለበላይ የህወሃት ሹማምንት በተደጋጋሚ ቢያስገቡም ሰሚ ማጣታቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ወደ መጣችሁበት ክልል ከመሄድ ውጭ ምንም የመፍትሄ ሐሳብ የለም መባላቸው ታውቋል። በጉዳዩ ዙሪያ የአማራ ክልል እና የአፋር ክልል ቱባ ሹማምንት መክረውበት ወደ ስምምነት ደርሰዋል መባላቸውንም ለማወቅ ተችሏል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ዘረኛው የህወሃት አገዛዝ በተለይ በአፋር እና በሶማሌ ክልል በተቋማት ተቀጥረው የሚሰሩ የአማራ ብሄረሰብ ተወላጅ ኢትዮጵያውያን "ከተቃዋሚዎች ጋር ይተባበራሉ፤ በህቡዕ ይሰራሉ" በሚል በስጋት ተወጥሮ እንደሚገኝ የታወቀ ሲሆን አሁን በአፋር ክልል የተጀመረው ኢትዮጵያውያኑን የማፈናቀል እንቅስቃሴ ቀጣይ መዳረሻው የሶማሌ ክልል ሊሆን እንደሚችል ተነግሯል። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ዘረኛው የህወሃት አገዛዝ በአፋር ክልል በሚገኙ ተቋማት ተቀጥረው፤ እንዲሁም በሃላፊነት ጭምር እንዲሰሩ የትግራይ ብሄረሰብ ተወላጅ ኢትዮጵያውያንን ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የወያኔ ቅጥረ ች ደቡብ ጎንደር ዉስጥ ከ 11 በላይ ንጹሃን ዜጎች በጥይት ተደብድበው ገደሉ

የጦር መሳሪያ ለማስፈታት በተለይ በአማራ ክልል በስፋት እየተንቀሳቀሰ የሚገኘው የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በደቡብ ጎንደር በስማዳ ወረዳ መሳርያ አላችሁ ፍቱና አስረክቡ በሚል ከህዝቡ የተነሳው አለመግባባት ወደ ግጭት በመለወጡ የአገዛዙ ቅጥረኛ ሚሊሻዎች በወሰዱት እርምጃ ከ 11 በላይ ንጹሃን ዜጎችን በጥይት ደብድበው መግደላቸው ታውቋል። ግጭቱን ተከትሎ በአካባቢው የነገሰው ውጥረት አሁን ድረስ አለመብረዱ የታወቀ ሲሆን የወረዳው ህዝብ ራሱን ለመከላከል እየወሰደ ባለው እርምጃ የተገደሉ የአገዛዙ ቅረኛ ሚሊሻዎች መኖራቸውንም ለማወቅ ተችሏል። አድማጮቻችንን በግጭቱ ዙሪያ መረጃ ለመሰብሰብ ወደ አካባቢው የተንቀሳቀሰው ዘጋቢያችን የሚያደርሰንን ዘገባ በሐሙሱ የዜና እወጃችን ይዘን የምናቀርብ መሆኑን ከወዲሁ ለማሳሰብ እንወዳለን።

በተያያዘ ዜና በምእራብ አርማጭሆ የመከላከያ ሰራዊትን በመክዳት የሚሰዎሩ ወታደሮች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱን ተከትሎ በአካባቢው የሚገኙት የአገዛዙ ቅጥረኛ አጋዚዎች በህዝቡ ላይ የአጸፋ እርምጃ እየወሰዱ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል። በአገዛዙ እየደረሰባቸው ባለው በደል የተማረሩት እነዚሁ የምእራብ አርማጭሆ ወረዳ ነዋሪዎች እሁድ እለት የተቃውሞ ሰልፍ ማድረጋቸው ታውቋል። የተቃውሞ ሰልፉ ምክንያት ጥቅምት 7 ቀን አንድ ወታደር መጥፋቱን ተከትሎ የአጎቱ ልጅ የሆነው የጤና ባለሙያ በአጋዚዎች ከፍተኛ ድብደባ ደርሶበት እንዲታሰር በመደረጉ እንደሆነ ተነግሯል። በአጋዚዎች የተደበደበው የጤና ባለሞያ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበት እንደሚገኝም ለማወቅ ተችሏል። ከወታደሩ መጥፋት ጋር በተያያዘ ሴቶችና ወንዶችም ተይዘው እየተደበደቡ ነው። የወረዳው ነዋሪዎች እንደሚሉት በአካባቢያቸው የሰፈረውን የመከላከያ ሰራዊት እየተው የሚጠፉ ብዙ ናቸው። ወታደሮቹ በጠፉ ቁጥር በነዋሪው ላይ የሚደርሰው እንግልትም በዚያው ልክ እየጨመረ በመሄዱ ከፉኛ መማረራቸውን ገልጸዋል። ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## እንግሊዝ ለወያኔ አገዛዝ ትሰጥ የነበረውን የደህንነት ማኔጅመንት ስልጠና ፕሮግራም አቋረጠች

በእንግሊዝ መንግሥት ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍ አማካኝነት ለፋሽስቱ ወያኔ ቱባ ሹማምንት፤ የደህንነት አካላትና ቅጥረኛ ካድሬዎች ጭምር በእንግሊዝ አገር ይሰጥ የነበረው የደኅንነት ማኔጅመንት የማስትሬት ፕሮግራም መቋረጡን የእንግሊዝ መንግሥት ዲፓርትመንት ፎር ኢንተርናሽናል ዴቨሎፕመንት (ዲኤፍአይዲ) አስታውቋል። የእንግሊዝ መንግስት ለፕሮግራሙ ማስፈጸሚያ ከ 70 ሚሊዮን ፓውንድ በላይ ወጭ ያደርግ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል።

የእንግሊዝ መንግስት ፕሮግራሙ የተቋረጠበትን ምክንያት ለጊዜው ይፋ ከማድረግ የተቆጠበ ቢሆንም የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በንጹሃን ዜጎች ላይ እያደረሰ ያለው መጠነ ሰፊ የሰብአዊ መብት ጥሰት፤ በልማት እንዲሁም ዘርን መሰረት በማድረግ ዜጐችን ለዘመናት ከኖሩበት አካባቢያቸው የማፈናቀል ወንጀል ተባብሶ በመቀጠሉ፤ በፖለቲካ መሪዎችና፤ አራማጆች እንዲሁም ጋዜጠኞችና ጦማርያን ላይ አገዛዙ እፈጸመ የሚገኘውን ወንጀል ተከትሎ ኢትዮጵያውያን የእንግሊዝ መንግስት ለፋሽስቱ ወያኔ እያደረገ ያለውን ድጋፍ እንዲያጤን በተደደጋጋሚ ግፊት በማድረጋቸው ሳይሆን እንደማይቀር በርካቶች ግምታቸውን ሰንዝረዋል። በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በተለይ የንቅናቄያችን ዋና ጸሐፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በየመንና ሰንአ አየር መንገድ በህገወጥ መንገድ ታፍነው ለጉጅሌዎቹ ተላልፈው ከተሰጡ በኋላ በእንግሊዝ መንግስት ላይ እያሳደሩት ያለውን ጫና አጠናክረው መቀጠላቸውም ለድጋፉ መቋረጥ አብይ ምክንያት ሊሆን እንደሚችልም ተገምቷል።

( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የወያኔ ዘረኞች በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚያደርጉትን የመሬት ዝርፊያ አጠናክረዉ ቀጥለዋል

የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ከአዲስ አበባ በቅርብ ርቀት ላይ በሚገኙ የኦሮምያ ልዩ ዞን እየተባለ በሚጠራው የለገጣፎ ለገዳዲ ከተማ የሚገኘው የአርሶአደሩ መሬት እየተነጠቀ በአገዛዙ ቱባ ሹማምንትና የቅርብ ዘመዶቻቸው ቁጥጥር ስር እየዋለ እንደሚገኝ ምንጮቻችን አመልክተዋል። በከተማው የሚታየውን የቦታ ዘረፋ በተመለከተ የከተማውና የገጠሩ ነዋሪ በጋራ በተደጋጋሚ የተቃውሞ ሰልፍ ማድረጋቸው የታወቀ ሲሆን ለችግሮቻቸው ግን መፍትሄ ፈጽሞ ማግኘት አለመቻላቸውን ለማወቅ ተችሏል። በአገዛዙ የተሾሙት የከተማው ካድሬዎች ጭምር በመሬት ዘረፋው ተሳታፊ መሆናቸው ታውቋል። በለገጣፎ ለገዳዲ በተለያዩ ተቋማት ሲያገለግሉ የነበሩ ጥቂት የማይባሉ የከተማው ተወላጅ ወጣቶች በአገዛዙና ቱባ ሹማምንት የሚፈጸመውን ዝርፊያ በማጋለጥ በኩል ከፍተኛ ሚና ሲጫወት ቢቆዩም በመጨረሻም ገሚሶቹ ለእስር የተቀሩት ደግሞ ለስደት መዳረጋቸውን ለማወቅ ተችሏል። ይህ በእንዲህ እንዳለ በሙስና ተከሶ በእስር የሚገኘው የቀድሞው የህወሃት ታጋይ ገብረውሃድ ወልደ ጊዮርጊስ በዚሁ በለገጣፎ ለገዳዲ የቦታ ካርታ በብዛት ካላቸው የህወሃት ቱባ ሹማምንቶች መካከል አንዱ መሆኑን ለማወቅ ችለናል።

## በአፋር የፌደራል ፖሊሶች አንድ ሰው ገድለው ሌላ ሰው አቆሰሉ

በወየኔ ዘረኞች የሚታዘዙ የፌዴራል ፖሊስ አባላት አፋር ክልል ዉስጥ አንድ ሰዉ ገድለዉ ሌላ አንድ ሰዉ ማቁሰላቸዉን የግንቦት ሰባት ምንጮች ከስሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ በላኩልን ዜና ገለጹ። ዘጋቢዎቻችን የአካባቢውን ምንጮች ጠቅሰዉ እንደተናገሩት በአሚባራ በአፋርና በኢሳ መካከል የተነሳውን ግጭት ተከትሎ የፌደራል ፖሊስ አባላት በወሰዱት እርምጃ አንድ ሰው ገድለው ሌላ የአፋር ተወላጅን ደግሞ አቁስለዋል። በአካባቢው ውጥረቱ አሁንም መቀጠሉን ገልጸዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከትናንት ጀምሮ ገዋኔና ቡድመዳ ወረዳዎች በጎርፍ መጥለቅለቃቸው ታውቋል። የአካባቢው ነዋሪዎች መንግስት በቂ ድጋፍ እያደረገ አይደለም በማለት ወቅሰዋል። በአዋሽ ቀበና ላይ የሚካሄደው የስኳር ፕሮጀክት እንዲሁም የመተሃራ የበሰቃ ውሃ ለአዋሽ ውሃ መሙላት መንስኤ መሆኑን የሚናገሩት ነዋሪዎች፣ በዚህም የተነሳ በህዝቡ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰ ነው ብለዋል።

## ባነሰ ወጪ ድልን መቀዳጃ አመቺ ጊዜ ላይ ነን - እንጠቀምበት !

በአለፈው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ በምንም የማይገናኙ እና የተመሰቃቀሉ የሚመስሉ፤ በጥልቀት ላያቸው ግን የተያያዙና የተደጋገፉ ከመሆናቸው አልፎ እንደከዋክብት ፈለግ አቅጣጫን የሚያመላክቱ በርካታ ክስተቶች ተስተውለዋል። የጊዜ ቅደም ተከተላቸውን ሳንጠብቅ አንዳንዱን ለአብነት ያህል እናንሳ።

በማኅበረ ቅዱሳን ላይ የዘነበው የዘለፋና የዛቻ ውርጅብኝ ህወሓት በቀጥታ በማይቆጣጠራቸው ማኅበራት ላይ ሁሉ ሲደርስ የቆየው ነፃ ማኅበራትን የማፍረስ ዘመቻ አካል መሆኑን መገንዘብ ቀላል ነው። ህወሓት የእስልምና እምነት ተከታዮችን ነፃ ማኅበርን በቁጥጥሩ ውስጥ ካስገባ በኋላ ፊቱን ወደ ክርስትና በተለይም ወደ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ማዞሩ የተረጋገጠ ነገር ሆኗል። ወያኔ በሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ ማንም ከጥቃት እንደማያመልጥ፤ ለምንም ጉዳይ ይቋቋም ወያኔ የማይቆጣጠረው ማኅበር እንዲኖር የማይፈልግ መሆኑ ከዚህ በፊት የሚታወቅ ቢሆን በድጋሚ ማረጋገጫ የሰጠበት አጋጣሚ ሆኗል።

በመዠንግር ከአስራ አምስት በላይ የሥርዓቱ ታጣቂዎች ከነመሣሪያዎቻቸው አገዛዙን ክደው ጠፍተዋል። የጠፉትን ለማደን የመጡ ወታደሮች ደግሞ ከሕዝቡ ጋር በፈጠሩት ግጭት በርካቶች ሕይወታቸውን አጥተዋል። በዚህ ግጭት ብቻ ከ40 በላይ ወታደሮች መገደላቸው ይነገራል። በጋምቤላ እና በቤንሻንጉልና ጉሙዝ ወረዳዎች ውጥረት ሰፍኗል። ከመሃል አገር ሄደው ኑሮዓቸውን እዚያው ያደረጉ ዜጎች ላይ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚደርስባቸው አፈናና እንግልት ጨምሯል። ግድብ እየተሠራበት ነው በሚባለው አካባቢም ከአሁኑ የፀጥታ ችግር እየደረሰ መሆኑ መረጃዎች ይጠቅማሉ። ወያኔ በምሥራቅ ኢትዮጵያ ኦጋዴን ውስጥ የገባበት ዓይነት ማጥ በምዕራብና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያም እየመጣ መሆኑ አመላካች ነው። የመከላከያ ሠራዊት አባላት መፍለስና የነፃነት ታጋዮችን መቀላቀል የእለት ለእለት ትዕይንት እየሆነ ነው። ወያኔ በመሃል አገር በሙስሊም እና በክርስቲያን ወገኖቻችን የእምነት ማኅበራት ላይ በከፈተው ግንባር "ጠብ ያለሽ በዳቦ" ሲል ዳር ዳሩን ሠራዊቱና ሕዝቡ ለማይቀረው ፍልሚያ እየተዘጋጁ ነው።

በርካታ ጋዜጠኞችና አሳታሚዎች ለስደት ከተዳረጉ ጥቂት ሣምታት በኋላ "የሚመጣውን ሁሉ አገሬ ውስጥ ሆኜ እቀበላለሁ" ያለውን ጋዜጠኛ ተመስገን ደሣለኝ አሳዛኝም አስቂኝም በሆኑ ክሶች ጥፋተኛ ተብሎ ወደ ወህኒ ተግዟል። በጋዜጠኞች ሕይወትና ሞት ወያኔ የፓለቲካ ቁማር መጫወቱ አጠናክሮ ቀጥሏል። በአንፃሩ ደግሞ በውጭ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያን አምርረዋል። የወያኔ ሹማምንት በአሜሪካ እና አውሮፓ የሚዘዋወሩት በሰቀቀን ሆኗል፤ በየደረሱበት ውግዘትና ውርደት ይጠብቋቸዋል። የወያኔ ሹማምንት በኢትዮጵያዊያን የተጠሉና የረከሱ ተደርገዋል።

የዩ.ኤስ. አሜሪካው ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ከኢትዮጵያ ቴሌቬዥን ባላነሰ ወያኔን በልማት አምጭነት አሞካሽተዋል። የአውሮፓ መንግሥታት በሰብዓዊ መብቶች አያያዝ ወያኔን እየተቹም ቢሆን ወያኔ በሚሰጣቸው ቁጥር እየማለሉ "እውነትም ልማት እየተፋጠነ ነው" በሚል ተስፋ ማበረታቻ እየሰጡት ነው። በዚህ ደስታ አቅሉን ያጣው ኃይለማርያም ደሣለኝ የውሸት ቁጥሮችን የመፈብረክ ሥራ ከስታትስቲክስ ጽ/ቤት ነጥቆ የራሱ የሥራ ድርሻ አድርጎታል። በዚህ አዲሱ ሥራውም ውጤት እያስመዘገበ ነው። ሁለት መቶ አምሳ (250) ሚሊዮን ኩንታል ሰብል አመረትን ባለ በሶስት ወሩ ሶስት መቶ (300) ሚሊዮን ኩንታል አመረትን በማለት በሶስት ወራት ውስጥ ብቻ የ20 በመቶ የግብርና ምርቶች የውሸት እድገት ፈጥሯል።

የውሸት ቁጥሮች ፈጠራ እንዲህ ቢፋፋምም፤ ቁጥሮቹን የሰሙ ኦባማ፣ የአውሮፓ መንግሥታት ሆነ ዓለም ባንክ ቢያወድሱትም አገር ውስጥ ያለው ሀቅ አልቀየረም። ስኳር፣ ዘይት፣ እንቁላልና ሌሎች የምግብ ግብዓቶች የደረሱት የሚያውቅ ጠፍቷል። ውሃ የለም፤ መብራት የለም፤ ኔት ዎርክ የለም። የአዲስ አበባ ጎዳናዎች በመቸውም በባሰ መጠን በነዳያን እና በቤት አልባ በረንዳ አዳሪ ዜጎች ተጥለቅልቀዋል። ድህነት ከጎጆዎች ወጥቶ ጎዳናዎች ላይ ፈሷል። የገንዘብ ዋጋ ወርዶ ወርዶ ብር ቁራጭ ወረቀትን ማከል አቅቶታል። በጥቂት በዝርፊያ በደለቡ የህወሓት ሹሞችና በብዙሃኑ ኢትዮጵያዊ መካከል ያለው የኑሮ ልዩነት ማነፃፀር እንኳን እንዳይቻል ሆኖ ተራርቋል።

የመከላከያ ሠራዊት አባላት በኑሮም በዘረኝነትም እየተማረሩ ነው፤ አለቆቻቸው ግን አሁንም በዝምድና እየተፈላለጉ እየተሿሿሙ ነው። አሁንም በዝምድና እየተፈላለጉ እርስ በራሳቸው እየተሿሿሙ ጄኔራሎች ሁሉ ዘመዳሞች ሆኑ፤ በሥራቸው ያለውን ኢትዮጵያዊውን ወታደር ግን እንደ ግል አሽከራቸው እንኳን ማየት ተጠይፈዋል። በጄኔራሎችና በሠራዊቱ መካከል ያለው ግኑኝነት ከጌታና ሎሌም የባሰም ሆኗል።

እነዚህ ምስቅልቅል ያሉ ሁኔታዎች ምንን ያመለክታሉ?

እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ምስቅልቅል ያሉ ሁኔታዎችን በጥንቃቄ የተነተነ ሰው በምስቅልቅነታቸው ፋንታ ሥርዓት የያዙ ፈለጎችን ያገኛል። ከእነዚህ ፈለጎች አንዱ የሚያመላክተው መጪዎቹ ጥቂት ወራት ለኢትዮጵያ ወሳኝ ጊዜያት እንደሚሆኑ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ምስቅልቅል ውስጥ ያለው ወያኔ ነው። ወያኔ፣ በድንገት አዕምሮዉን እንደሳተ ሰው ይይዘው ይጨብጠው ጠፍቶታል። በዚህ ምስቅልቅል ወቅት ውስጥ በቢሊዮን የሚገመት የሕዝብ ሀብት አውጥቶ፤ የማይረቡ ድርሳናትን ጽፎ የአገሪቱን ዜጋ በሙሉ ካላሰለጠንኩ ሞቼ እገኛለሁ ማለቱ ራሱ የውስጡን መመሰቃቀል ማሳያ ነው። ሰልጠናውን ሰልጣኞች ብቻ ሳይሆን አሰልጣኞችም ጭምር የጠሉት ቢሆንም ፋታ የሚሰጠው መስሎት ገፍቶበታል። የነፃነት ኃይሎች በሚቀጥሉት ጥቂት ወራት ውስጥ ኃይላችንን አሰባስበን ከገጠምነው ባነሰ ወጪ ድልን መቀዳጃ አመቺ ጊዜ ይሆናል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ያለንበት ወቅት ወሳኝነት በመገንዘብ ከመሰል ድርጅቶች ጋር ውህደት በመፍጠር፤ ከሌሎቹ ጋር በጥምረት ትግሉን ለማፋጠን ቆርጦ ተነስቷል። የኢትዮጵያ ሕዝብ የወቅቱን ልዩ ባህሪ በመገንዘብ በአንድ ልብ ለትግል እንዲነሳ ግንቦት 7 ጥሪ ያቀርባል።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

## የወያኔ ዘረኞች በአማራ ተወላጆች ላይ የከፈቱትን ዘመቻ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በመመደብ ላይ መሆኑን ተከትሎ በክልሉ በተለያዩ ሞያዎች በመጀመሪያ ዲግሪና በሁለተኛ ዲግሪ የተመረቁ የብሄረሰቡ ተወላጅ ምሁራን ጭምር ስራ የማያገኙበት ሁኔታ መኖሩን ነዋሪዎች አመልክተዋል። የክልሉን የንግድ ዘርፍም በበላይነት የተቆጣጠሩት ከአንድ ብሄረሰብ የተውጣጡ የአገዛዙ ቅጥረኛ ባለሃብቶች መሆናቸውን ተከትሎ አፋሮች ክልላችን የዘረኛው ህወሓት አገዛዝና ቅጥረኛ ባለሃብቶች መጫዎቻ ሆኗል ሲሉ ምሬታቸውን እየገለጹ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል።

ዘረኛው የህወሓት አገዛዝ የአፋርን ክልል ህዝብና ቱባ ሹማምንቱን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር በተለይ በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ውስጥ በርካታ ካድሬዎቹን አሰማርቶ የስለላ ስራ እየሰራ እንደሚገኝም በተለያየ ጊዜ መዘገቡ ይታወሳል። የስለላ ቡድንኑን በበላይነት እየመራ የሚገኘው ሚካኤል የሚባል የቀድሞ የህወሃት ታጋይ ሲሆን ይህ ዘረኛ ግለሰብ ህወሃት ክልሉን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር እያደረገ ያለውን ሴራ በማስፈጸም ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል። የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በክልሉ አፋሮችን ከከተማ አካባቢዎች እያስወጡ ወደ ገጠር በመመለስ ስራ ላይ መጠመዳቸውም መዘገቡ አይዘነጋም።

## እንግሊዝ ለወያኔ አገዛዝ ትሰጥ የነበረውን የደህንነት ማኔጅመንት

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን በውንብድና ከየመን ሰነአ አየር ማረፊያ አሳፍነው መውሰዳቸውን ተከትሎ መቀመጫውን ለንደን ያደረገው ነፃ የሕግ አገልግሎት የሚሰጠው ተቋም ሪፕሪቭ፤ የአውሮፓ ኅብረት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን እንዲሁም የተለያዩ አለማቀፍ ተቋማትና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች የእንግሊዝ መንግስት ከአገዛዙ ጋር ያለውን ግንኙነት፤ እንዲሁም እያደረገ ያለውን ድጋፍ እንዲያጤን አበክረው እየጠየቁ እንደሚገኙም በተለያዩ ጊዜያት መዘገቡ አይዘነጋም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ለደህንነታቸው ሲባል ስማቸው የማይጠቀስ አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር ጉዳዩን በማስመልከት ለሬዲዮ ክፍላችን በላኩት አስተያየት የእንግሊዝ መንግስት የወሰደውን እርምጃ በማድነቅ የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ ከተለያዩ አለማቀፍ መንግስታት የሚያገኘው ድጋፍ የአገዛዙንና የቱባ ሹማምንቱን ኪስ ከማድለብ በዘለለ ለጭቁኑ የኢትዮጵያ ህዝብ አንዳችም የፈየደለት ነገር የለም፤ ይልቁንስ ለአገዛዙ እየተደረገ ያለው ድጋፍ አምባገነናዊ ጡንቻው እንዲያፈረጥም በማስቻል አገራችንን አሁኑ ለገባችበት የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ምስቅልቅል ዳርጓታል ሲሉ አስተያየታቸውን አድርሰውናል።

# ህወሃትና የጦር አበጋዞቹ እሴቶች

ህወሃት የትግሬ ተወካይ ብቻ ሳልሆን ለትግራይ ህዝብ የሚያመልከውን አምላክም ጭምር የምመርጥለት እኔ ነኝ በሚል እብሪት ውስጥ ይገኛል። በዚህ እብሪቱም እየተመራ የምታመልኩትን ልመርጥላችሁ ብሎ አጠቃላይ ሙስሊሙንም ክርስትያኑንም እያመሰው እንደሆነ እያየን ነው። እኔን የማይቀበል እጣ ፈንታው ከመታመስ በላይ የሆነ ወዮታ ነው የሚል ያልተፃፈ አዋጅም አለው። ህወሃት በትግራይ ትከሻ ላይ ተፈናጦ፤ ትግራይን ምርጫ አሳጥቶ እኔን እምኑ መንገዳችሁም ህይወታችሁም እኔ ብቻ ነኝ ብሎ ራሱን የትግራይ ጣዖት አድርጎ ሹሟል። ይሄን ጣዖት አንቀበልም፤ እኛ የራሳችን ሂሊና ያለን እንደ ሰው ማሰብ የምንችል ነን ያሉ ብዙ የኢትዮጵያ ልጆች ባልታወጀው አዋጅ መሠረት አብዮታዊ ፀሎት እየተፀለየላቸው አፈር ለብሰው ቀርተዋል።የህወሃት የእብሪቱ መጀመሪያ "እኔ ያልኩት ካልሆነ ሁሉም ገደል ይግባ" ማለቱ ነው። የትግራይ ተወካይ እኔ ብቻ ነኝ ሌላው ሁሉ የትግራይ ህዝብ ጠላት ነው የሚል እምነቱ የድርጅቱን ሥር የሰደደ መሠሪነትና እብሪት የሚያሳይ ነው።

ብዙ ኢትዮጵያዊያን ህወሃት የቆመው ለትግራይ ህዝብ ነው የሚል ዕምነት አሳድረዋል። ይሄን አስተሳሰብ መቀበል የሚጠቅመው ለህወሃት ብቻ ነው።ህወሃት ለትግራይ ህዝብ ክብርም ፍቅርም ያለው ቡድን አይደለም። ለትግራይ ህዝብ በጎ ምኞት እና ክብር ያለው ቢሆን ኑሮ የትግራይ ህዝብ የወደደውን እንዲመርጥ፤ ያልወደደውን እንዲተው ያልተሸራረፈ ነፃነት እንዲኖረው ያደርግ ነበር። እኛ እንደምናየው ግን የትግራይ ህዝብ የወደደውን ለመምረጥ፤የጠላውን ለመተው እንዲችል ነፃነትያለው ህዝብ አይደለም። የትግራይ ህዝብ ነፃነቱን በነፃነት ሥም ያጣ ህዝብ ሁኗል። ህወሃቶች የትግራይን ህዝብ ነፃነት ሸራርፈው ሸራርፈው ህዝቡን በሙሉ መያዣ አድርገውና ከወገኑ ለይተውት እየገዙት ይገኛሉ። የትግራይም ህዝብ ሳይወድ በግዱ ህወሃቶችን ተሸክሞ መከራው በዝቶ እየተገዛ ይገኛል።

ህወሃት መራሽ በሆነው መከላከያ ድህረ-ገፅ ላይ "ያልተሸራረፈ ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ማስረፅ" እሴታችን ነው የሚል መፈክር በጉልህ ተፅፏል። ህወሃቶች መከላከያ ኃይሉ የቆመው የህዝቡን ያልተሸራረፈ ዲሞክራሲዊያ አስተሳሰብ ለመንከባከብ ነው እያሉን ነው። የህዝቡ ዲሞክራሲያዊ መብት ሳይሸራረፍ ተከብሮ ቢሆን ኑሮ ጋዜጠኛ ሚሊዮን ሹርቤ ተሰዶ ሂዶ በባዕድ አገር ባልሞተ ነበር። ህዝቡ በኑሮ ውድነት ባልተሰቃየ ነበር፤ አገሪቷ ሠላም ርቋት እዚህም እዚያም የዜጎች ደም በከንቱ ባልፈሰሰ ነበር፤ የአገሪቷ ብሄራዊ አንድነት ላልቶ ዜጎች ይሄ ክልል አገራችሁ አይደለም እየተባሉ ከኖሩበት መንደር ውጡ ባልተባሉ ነበር፤ ዜጎቿ አገር ውስጥ ከመኖር ይልቅ በባህር ውስጥ አዞ መበላትን ምርጫቸው ባላደረጉ ነበር። አገሪቷ እንዲህ ምስቅልቅሏ ወጥቶ ባለበት ሁኔታ ህወሃቶች ያልተሸራረፈ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብን መንከባከብ የሚችል ሠራዊት ገንብተናል እያሉ እያላዘኑ ይገኛሉ። ይሄንንም ለማጠናከር ስንል የጦር አበጋዞችን መሾም አስፈልጎናል ብለው የአንደኛ ደረጃ ፊደል ቆጥረው ያልዘለቁ ሽፍቶችን ሹመት በሹት እያደረጓቸው ነው።

"ዘላለማዊ ክብር" በሰይጣን መንፈስ ሲመራ ለነበረው ለመለስ ዜናዊ ይገባል ብሎ የሚያመነው "ክርስትያኑ" ደሳለኝ ኃ/ማሪያም በመለስ ዜናዊ መንፈስ እየተመራ ስልጣኑን ከያዘ ግዜ ጀምሮ 4 ሌተናል ጄኔራሎች፤ 9 ሜጀር ጄኔራሎች፤ 28 ብርጋዴር ጄኔራሎችን ሹሟል። ብዙ ሰዎች ግን ደሳለኝ ኃ/ማሪያም በዚህ ሹመት ውስጥ የመወሰን ድምፅ የለውም ይላሉ። እንዲያውም ደሳለኝ የነብሩን ጭራ ይዞ እንዳይለቀው ጭንቅ ሆኖበት የሚኖር ብኩን ግለሰብ ነው ሲሉም ያክላሉ። ያም ሆነ ይህ ደሳለኝ ኃ/ማሪያም የመለስ ዜናዊን ራዕይ ሊያስፈፅም በትር ስልጣኑን ጨብጧልና በእርሱ ዘመን ለሚሆነው ሁሉ ኃላፊነት ይወስዳል።

ወደ ጦር አበጋዞቹ እንመለስ ከእነዚህ የጦር አበጋዞች መካከል አብዛኞቹ የህወሃት አባሎች መሆናቸው የታወቀ ነው። በዚህ ጥቅምት ወር ብቻ 3 ሌተናል ጄኔራሎች እና 3 ሜጀር ጄኔራሎች ተሹመዋል። እነዚህ የጦር አበጋዞች በየትኛው መደበኛ ጦር አውድማ ላይ ውለው ለዚህ ማዕረግ የሚያበቃቸውን ምግባር እንደፈፀሙ የሚያውቅ የለም። ሽፍቶች እና ጎሬላ ተዋጊዎች መሆናቸው ግን የሚካድ አይደለም። የሽፍትነትና የጎሬላ ውጊያ ልምድ ግን ለዚህ ማዕረግ የሚያበቃቸው ሊሆን እንደማይችል የታወቀ ነው።

ሌተናል ጄኔራል ሁነው ከተሾሙት መካከል

1ኛ. አብርሃም ወ/ማሪያም
2ኛ. አደም መሃመድ
3ኛ. ብርሃኑ ጁላ

ሲሆኑ ወደ ሜጀር ጄኔራልነት ያደጉት ደግሞ

1ኛ. ክንፈ ዳኘ
2ኛ. ተክለብርሃን ወ/አርጋይ
3ኛ. ዘውዱ እሸቴ ይባላሉ።

የእነዚህ የጦር አበጋዞች ሹመት ባላቸው የትምህርት ደረጃ፤ ለህዝባቸው ባላቸው ክብር፤ ለአገራቸው ባላቸው ፍቅር ሳይሆን ለጣዖቱ ህወሃት ያላቸው ታማኝነት ሚዛን ደፍቶ በመገኘቱ ነው።

ከስድስቱ የጦር አበጋዞች መካከል የአራቱ ሹመት ቤተሰባዊ ዝምድናን መሠረት ያደረገ ስለመሆኑ የሚከተለውን ትሥሥር እንድትመለከቱ እንጋብዛላእን።

1ኛ. በሌተናል ጄኔራልነት ማዕረግ የተሾመው አብርሃም ወ/ማሪያም የመለስ ዜናዊ የሥጋ ዘመድ ነው። የመለስ ዜናዊ ቅደመ አያት በጎን ከሌላ ሴት የወለዷቸው ሴት ልጅ ልጅ ነው።
2ኛ. ሜጀር ጄኔራል ክንፈ ዳኜ ደግሞ አባቱ አቶ ዳኜ ገ/ስላሴና የመለስ አባት የአቶ ዜናዊ እናቶች እህትማማቾች ናቸው።
3ኛ. ሜጀር ጄኔራል ዘውዱ እሸቴ ደግሞ የመለስ ዜናዊን የቅርብ ዘመድ አግብቶ በጋብቻ ተሳስሯል። ሚስቱ ደግሞ በ18 ዓመት ታንሰዋለች።
4ኛ. ሜጀር ጄኔራል ተክለብርሃን ወ/አረጋይ የመለስ ዜናዊ የአክስት ልጅ ነው።

ይህ መከላከያ ኃይል ተብሎ የአንድን ጎጠኛ ድርጅት ህልውና ለመጠበቅ የቆመውን ቡድን የሚመሩት የጦር አበጋዞች በትምህርት ደረጃቸው ከሚያዟቸው ተራ ወታደሮች የማይሻሉ፤ ከራሳቸው ወዲያ ህዝብና አገር የሚባል ነገር የማያውቁ፤ በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ የአገሪቷን ሃብት ለመዝረፍ የሚሽቀዳደሙ እና ራሳቸውን እንደ ኢንቨስተር የሚቆጥሩ፤ የውትድርናን ሙያ ከነፍስ ግዲያና ከጭካኔ ለይተው የማያዩ እና ርህራሄ የሌላቸው ስለመሆናቸው የህወሃት ድርሳናት ይመሰክራሉ።

ህወሃት ርህራሄን የማያውቁ ጭካኞችን የጀግንነት ማዕረግ እየሰጠ በአገሪቷ ላይ እያሰማራ ይገኛል። የህወሃቶች ስነ-ምግባርም ሆነ ስነ-ልቦና ለጀግንነት የሚያበቃቸው አይደለም። በህወሃት መንደር ጀግናና ጀግንነት አይታወቁም። ጀግና እውነትን አይፈራም። ህወሃት እውነትን ስለሚፈራ ገና ድክ ድክ የሚሉ ነፃ ሚዲያዎችን ያለ ምንም ማወላወል ሊደመስሱ የሚሽቀዳደሙትን ይሾማል። ጀግና ነፃ ሚዲያን የሚፈራበት ምንም ምክንያት አይኖረውም። ጀግና ነፍሰ ገዳይ አይደለም። ህወሃት ህፃን ነብዩን የመሰሉ እንቦቀቅላዎችን ግንባር ግንባራቸውን ብለው ለመግደል የማይራሩ ጨካኞችን ይሾማል። ጀግና ሌብነትን ከልቡ ይፀየፋል። ህወሃት ግን ሌብነትን የሚፀየፉትን ሳይሆን የድሃ ንብረት ሰርቆ ሃብት ማካበትን እንደ ብልጠት የሚቆጥሩ ደካሞችን ጄኔራል እያለ ያሰማራል።

በዚህ በጥቅምት ወር የተሾሙት 6 የጦር አበጋዞች ለሹመት ሲታጩ የትምህርት ዝግጅታቸውና ብቃታቸው፤ ለአገራቸው ያደረጉት የላቀ አስተዋፅዖ፤በውጊያ አውድማ ያሳዩት ጀግንነት ታይቶ ነው የሚል ወሬ ከህወሃት መንደር ተሰምቷል። ህወሃቶች እና ደጋፊዎቻቸው ይሄን ለማመን አይቸገሩም። የእነዚህ ቡድኖች ዋና መለያ የገዛ ውሸታቸውን እውነት ነው ብለው አምነው ጥሩ እንቅልፍ መተኛት የሚችሉ መሆናቸው ነው። የገዛ ውሸቱን እውነት ነው ብሎ የሚያምን ግለሰብ ብርቱ የሆነ የስነ-ልቦና ቀውስ ውስጥ የወደቀ መሆንኑ የስነ-አዕምሮ ተማራማሪዎች ይናገራሉ። ህወሃቶችም ብርቱ በሆነ የስነ-ልቦና ቀውስ ውስጥ እንደሚገኙ ለማየት የዕለት ተዕለት ውሽቶቻቸውን እና የሚፈፀሙትን ፀያፍ ድርጊቶች ማየት በቂ ይሆናል።

የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል በጥቂት በዘረ ሃረጋቸውና በቤተሰብ ክር በተሳሰሩ ወንበዴዎች እጅ ወድቋል። በእነዚህ ዘራፊዎች የሚመራ የሠራዊት ኃይል የህዝቡን ዲሞክራሲያዊ መብት ማስከበር አይቻለውም። የጦር አበጋዞቹ የአገሪቷን አንጡራ ሃብት እየዘረፉ ከገነቧቸው ህንፃዎች በየወሩ የሚሰበስቡትን ገንዘብ የሚጠይቅ ለህዝብ ወገንተኛ የሆነ መንግስት እንዲመሰረት ምንም ፍላጎት አይኖራቸውም። ለእነዚህ ጦር አበጋዞች ነፃነት፤ ፍትህ፤ እኩልነት እና እውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚባሉ ነገሮች ያሸብሯቸዋል። እነዚህንም ጥያቄዎች ያነሳ አሸባሪ ተብሎ የዚህን ምድር ሥቃይ እንዲያይ ይደረጋል።ይሄ ቡድን ሥልጣን ላይ እስከቆየ ድረስ ነፃነት ፤የህግ የበላይነት፤ እኩልነት የሚባሉ እሴቶች በኢትዮጵያ ይሰፍናሉ ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው።

በመጨረሻም ተራው ወታደር እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ነፃነቱን ተገፎ ለምንና ለማን እንደሚገልና እንደሚሞት ሳያውቅ በገዛ ወገኖቹ ላይ እየተኮሰና የንፁህ ደም እያፈሰሰ እንደሚኖር እያየን ነው። ተራው ወታደር ጋምቤላ ሂዶ ያገኘውን ሁሉ የሚገድለው ለምንድ ነው? ኦጋዴን ሂዶ የዘር ማጥፋት ወንጀል የሚፈፅመው ለምንድ ነው? ጉራፋርዳ ወርዶ የመዥንግሮችን ደም የሚያፈሰው በምን ምክንያት ነው? ያልተሸራረፈ ዲሞክራሲን አስፍነናል ከተባለ ይሄ ሁሉ ውጊያ ምንጬ ምንድ ነው? ሠራዊቱ ለእነዚህና ለመሰል ጥያቄዎች በቂ መልስ መፈለግ ይኖርበታል።ምንም ትርጉም በሌለው ውጊያ ውስጥ እየሄደ የንፁህ ደም ማፍሰሱን ለማቆምና ነገ በወንጀል ከመጠየቅ ራስንም ለማዳን ሠራዊቱ ራሱን ከዘረኞቹና ከዘራፊዎቹ የጦር አበጋዞች መለየት ይኖርበታል።ከእርሱ በሞራልም ሆነ በትምህርት ደርጃቸው ከማይሻሉ ጄኔራል ተብየዎች ራሱን ለይቶ ለነፃነት፤ ለፍትህ እና ለእኩልነት ከሚታገሉ ኃይሎች ጎን እንዲሰለፍ ጥሪያችንን አሁንም እናስተላልፋለን።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !

## ወያኔ ተቃዋሚዎችን በ"ሽብር" ስም ከጎረቤት አገሮች ለማሰር የሚያስችለዉን አዋጅ ለፓርላማ አቀረበ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የሚቃወሙትን የፖለቲካ ኃይሎች የገቡበት ቦታ ሁሉ ገብቶ ለማሰር የዋጣዉን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለዉን ረቂቅ ረቂቅ አዋጅ አርቅቆ ለዚያ ለሚቆጣጠረዉ ፓርላማ መላኩ ተሰማ። አዋጁ ሁለት ሀገራት በወንጀል የጠረጠሩትን ዜጎች በመያዝ ለፈላጊው ሀገር አሳልፎ ለመስጠት የሚያስችላቸው ነው። በረቂቅ አዋጁ ላይ እንደተመለከተው በዚህ ትብብር መሰረት መረጃው በሚፈለገው ሀገር አግባብነት ባለው ተቋም ህጋዊ መጠየቂያ ደብዳቤ መሰረት ለተጠያቂው ሀገር በመላክ ይከናወናል ይላል። ስምምነቱ በተጠርጣሪ ወንጀለኞች ጉዳይ ማስረጃዎችን የመሰብሰብ፣ ቃል የመቀበል፣ የሚያዙ ሰዎችን ወይንም ምስክሮች ለትብብር ጠያቂው ሀገር የፍርድ አካላት የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ የማድረግ፣ የፍርድ ሰነዶችን ለተጠርጣሪዎች የማድረስ፣ የንብረት ብርበራ ማድረግና መያዝ፣ የወንጀል ፍሬነገሮችን በመለየት የሚያዙበት፣ የሚታገዱበትና የሚወረሱበት ሁኔታ የማመቻቸት፣ የተጠርጣሪ ግለሰቦች ግንኙነት የመጥለፍ፣ በወንጀል ሒደት ውስጥ ሰርጎ በመግባት የወንጀል መረጃዎችን የማሰሰብና በጊዜያዊነት ለወንጀል ስራ የተያዙ ሰዎችን አሳልፎ የመስጠት ትብብሮችን ያጠቃልላል። ሁለቱ ሀገራት እ.ኤ.አ ዲሴምበር 4/2013 በሱዳን ካርቱም ከተማ በሱዳንና በኢትዮጵያ መካከል በወንጀል ጉዳዮች ላይ የጋር ትብብር በፈጸሙት ስምምነት መሰረት ይህ አዋጅ መቅረቡ ታውቋል።

ረቂቅ አዋጁ አራት ክፍሎች፣ 26 አንቀጾች ያካተተ ሲሆን ፓርላማው ለዝርዝር ዕይታ ለሚመለከተው ኮምቴ የመራው ሲሆን በቅርቡ ይጸድቃል ተብሎ ይጠበቃል። የኢትዮጵያ መንግስት የሚቃወሙትን ሃይሎች አነግ፣ ኦብነግ፣ ግንቦት ሰባት፣ የሻዕቢያ ቅጥረኛ የሚሉ ታፔላዎችን በመለጠፍና በሽብር ጠርጥሬያቸዋለሁ በማለት በጎረቤት ሀገራት በጥገኝነት እንዳይኖሩ ከፍተኛ ገንዘብ በመመደብ እያሳደደ፣ አንዳንዶቹንም እያሰረ መሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ ውግዘት እያስከተለበት እንደሚገኝ ይታወቃል።

የወያኑ አገዛዝ ሱዳን ለተቃዋሚዎች የመንቀሳቀሻ ቦታ እንዳትሰጣቸው ለማድረግ የአገሪቱን ሰፊ መሬት አሳልፎ መስጠቱን ተችዎች ይገልጻሉ። የምእራብ አርማጭሆ የአንድነት ፓርቲ ተወካይ አቶ አንጋው ተገኝ  የሱዳን ታጣቂዎች በድንበር አካባቢ የሚፈጽሙት ወንጀል እየባዛ ነው በማለት ተናግረዋል።

## የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች የትብብር ስምምነት ተፈራረሙ

ዘጠኝ የኢትዮጵያ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ጥቅምት 11/2007 ዓ.ም በሰማያዊ ፓርቲ ጽ/ቤት የትብብር ስምምነት መፈራረማቸውን ነገረ ኢትዮጵያ ዘግቧል።ፓርቲዎቹ ነጻ አሳታፊና ታአማኒ ምርጫ እንዲካሄድ በትብብር ለመስራት፣ የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋትና የዜጎችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ በጋራ ለመታገል መስማማታቸውን ትብብር ሰነዱ ላይ አስፍረዋል።

ትብብሩን እንዲመሩ  ኢንጅነር ይልቃል ጌትነት ከሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር፣ አቶ ኤርጫፎ ኤርጌሎ ከከንባታ ህዝቦች ኮንግረንስ ምክትል ሊቀመንበር፣ አቶ ግርማ በቀለ ከኦሞ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት ዋና ጻሃፊ፣ አቶ ካሳሁን አበባው ከመኢአድ ምክትል ዋና ጻሃፊ እንዲሁም አቶ ኑሪ ሙደሂር ከመኢዴፓ ገንዘብ ያዥ ሆነው ተመርጠዋል። አንድነትና መድረክ ውስጥ የታቀፉት ፓርቲዎች ትብብሩን ለመፈረም በየድርጅቶቻቸው ውሳኔ ባለመተላለፉ አለመፈረማቸውን ነገረ ኢትዮጵያ ገልጾ፣ ይሁን እንጅ ፓርቲዎቹ የትብብር ስምምነቱን ይፈርማሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ ጠቁሟል።

## የወያኔ ቅጥረች ደቡብ ጎንደር ዉስጥ ከ 11 በላይ ንጹሃን ዜጎች

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በሌላ ዜና የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ በቅርቡ በስደት በሚኖርበት የኬንያ ምድር ህይወቱ ያለፈውን የማራኪ መጽሄት ባለቤት እና ማኔጂንግ ዳይሬክተር የነበረውን የጋዜጠኛ ሚሊዮን ሹሩቤ አስከሬን ወደ አገር ቤት በማስገባት ለፖለቲካ ፍጆታው እየተጠቀመበት መሆኑ ኢትዮጵያውያንን ማስቆጣቱ ታውቋል። አገዛዙ በቅርቡ ጋዜጦችንና የህትመት ውጤቶችን በመዝጋት በተለይ በጋዜጠኞች ላይ የፈጠራ ክስ በመለጠፍ ወደ እስር ለማጋዝ መንቀሳቀሱን ተከትሎ ለስደት ከተዳረጉት ከ 23 በላይ ጋዜጠኞች አንዱ የነበረው ሚሊዮን ሹርቤ፤ በቅርቡ በስደት በሚኖርበት ኬንያ ባልታወቀ ምክንያት ህይወቱ ማለፉ ይታወቃል። የወያኔው ጉጅሌ አገዛዝ ጋዜጠኛውን በህይወት በነበረበት ወቅት በገዛ ሃገሩ ላይ እንዳይኖር ከፍተኛ ጫና በማሳደር ሃገሩን ጥሎ እንዲሰደድ ካደረገ በኋላ አስከሬኑን ወደ ሀገርቤት በማስገባት የፖለቲካ ቁማር ለመቆመር ሙከራ ማድረጉ በርካታ ኢትዮጵያውያንን አስቆጥቷል።የጉጅሌው አገዛዝ የሟቹ አስከሬን ቦሌ አለማቀፍ አየር ማርፊያ በደረሰበት ወቅት አውራምባ ታይምስ በተባለ ልማታዊ ጋዜጣ አማካኝነት የሟችን እህት እና ባለቤቱን አነጋገርኩ በማለት ይፋ ያደረገው መልእክት በርካቶችን ያሳዘነና ያስቆጣ አሳፋሪ ድርጊት እንደሆነ በርካቶች አስተያየታቸውን ሰተዋል። በሪፖርቱም ሚሊዮን ከአገዛዙ ጋር ምንም አይነት ችግር እንዳልነበረውና፤ ለስደት የተዳረገውም የቤተሰቦቹን ኑሮ ለመለወጥ በማሰብ እንደሆነ መገለጹ አስተዛዛቢ ነው ሲሉ መናገራቸው ታውቋል። የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በፍትህና መልካም አስተዳደር እጦት እራሱን በእሳት በማቃጠል መስዋዕት የሆነውን የመምህር የኔሰው ገብሬ ቤተሰቦችን በማስፈራራት እና በማስገደድ  በጥቅም በመደለል የኔሰው ገብሬ የአእዕምሮ ህመምተኛ ነበር ሲሉ አገዛዙ እንዳሻው በሚቆጣጠረው ቴሌቪዥን ቀርበው ምስክርነት እንዲሰጡ መደረጋቸው አይዘነጋም።

## ወያኔ ያሰለጠናቸዉ የሳይበር ተሳዳቢዎች  በማህበራዊ ድረ ገጾች ላይ ሊዘምቱ ነው

ተቃዋሚ ድርጅቶችን በሀሳብ ደረጃ ፊት ለፊት መጋፈጥ የተሳነዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የህዝብና የአገር ገንዘብ አባክኖ ያሰለጠናቸዉን ተሳዳቢዎች በየማህበራዊ ሜድያዉና በየድረገጹ ላይ እየሄዱ የስድብ ናዳቸዉን እንዲያወርዱ ተልዕኮ እንደሰጣቸዉ ታወቀ።  በሬድዋን ሁሴን የሚመራው የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት አሰልጥኖ በፌዴራል የመንግስት ተቋማት በህዝብ ግንኙነት ኃላፊነት ለመደባቸው ካድሬዎች የሁለት ቀናት የማህበራዊ ድረገጾች አጠቃቀም ስልጠና በመስጠት በተለይ በግንቦት ወር ከሚካሄደው ሀገር አቀፍ ምርጫ እንዲሳካ የበኩላቸውን አዎንታዊ ሚና እንዲጫወቱ አደራ ተጥሎባቸዋል።

የአዲስ አበባው ዘጋቢያችን እንደገለጸው የኮምኒኬሽን ጽ/ቤቱ በሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 158/2001 ሲቋቋም በመንግስትና በሕዝቡ መካከል ቀልጣፋ ውጤታማ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ማስቻል አንዱና ዋና ዓላማው ያደረገ ቢሆንም በተግባር ግን የሰለጠኑና ልምድ ያካበቱ የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያዎችን የአመለካከት ችግር አለባቸው በሚል በማባረርና በማንሳፈፍ ካድሬዎችን በለብለብ ስልጠና ሲመድብ ቆይቷል። ዘርፉ ልምድና በቂ ስልጠና በሌላቸው ካድሬዎች በመያዙ በመረጃ አሰጣጥ በኩል ያለው ችግር እንዲባባስ ምክንያት ሆኗል።

ጽ/ቤቱ የመደባቸው ካድሬዎች በተለይ በማህበራዊ ድረገጾች አጠቃቀም ደካማ በመሆናቸው ምክንያት ሚኒስትሩ አቶ ሬድዋን በሰበሰቡዋቸው ቁጥር ከፍተኛ ብስጭት የኢህአዴግን አቁዋም እንኩዋን መናገር የማይችሉ በማለት እስከመዝለፍ ደርሰዋል።

የዜና ምንጮቻችን እንደጠቆሙት በአዲስአበባ ቦሌ አካባቢ በሚገኘው ዋሽንግተን ሆቴል ባካሄደው ስልጠና ካድሬዎቹ እንደፌስ ቡክና ቲዎተር ባሉ ማህበራዊ ድረገጾች ላይ እንዴት መጠቀም እንደሚችሉና የመ/ቤታቸውንና የመንግስትን አቋም ከማስረዳት ባለፈም ጸረ መንግስት አቋም ያላቸውን መረጃዎች በማጣጣልና በማስተባበል ረገድ የበኩላቸውን የተከላካይነት ሚና እንዴት እንደሚወጡ በመሰልጠን ላይ ናቸው። በተለይ የማህበራዊ ድረገጾች መንግስትን በሚቃወሙ ሃይሎች ሙሉ በሙሉ ቁጥጥር ስር እንደወደቀ የአቶ ሬድዋን ቢሮ የሚያምን ሲሆን ይህን ለመመከት የሚያስችል ብቃት ያለው የኮምኒኬሽን ባለሙያ ባለመኖሩም ካድሬዎቹ በተደጋጋሚ ወቀሳ ሲሰነዝርባቸው መቆየቱን ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች  ለዘጋቢያችን ተናግረዋል። በአሁኑ ወቅት የአንዳንድ የፌዴራል መ/ቤት ተቋማት የህዝብ ግንኙነት ከፍተኛ ካድሬዎች በተለይ በፌስቡክ ፈራተባ እያሉ መረጃዎችን መልቀቅና በሚጻፉ የተለያዩ ጉዳዮች አስተያየት መሰንዘር በመለማመድ ላይ ናቸው።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ  የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB  በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና  በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ  5980 KHz እና  በ 60 MB  4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org